


## የሀዘን መግለጫ መልዕክት ስለ ዕዉቁ የጥበብ ሰው ክቡር ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ

ታላቁ የዘመናችን የዘፈን ንጉሥ ዝነኛው ክቡር ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ ሚያዝያ 12 ቀን 2001 ዓ.ም.ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱን የሰማነው በጥልቅ ሀዘን ነው።
ለሁላችንም በተራ የሚደርሰው “ አፈር ነህና ወደ መሬት ትመለሳልህ ...“ የሚለውና የማይሻረው የአምላክ ቃል በእዚህ ታላቅ የጥበብ አባት ላይም ተፈጻሚ መሆኑን ስለምንረዳና እንዲሁም ሙያውና ሥራው ደግሞ ለዘላለም ከመቃብር በላይ ከእኛ ጋር ስለሚኖርልን በዚሁ እየተጽናናን፤
ለሟቹ ወገናችን ነፍሱን ይማርልን፣ እንዲሁም ለቤተሰቡና ለመላው አፍቃሪ ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ደግሞ እግዚአብሔር ያጽናችሁ በማለት የፀጋዬ ደረ-ገጽ አዘጋጆች የሀዘናችሁ ተካፋይ መሆናችንን በአክብሮት እንገልጻለን!!!

ፀጋዬ ደረ-ገፅ ዝግጅት ክፍል
http://tsegaye.ethio.info
ሚያዝያ 15 ቀን 2001 ዓ.ም.